የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር ETHIOPIAN Computers & Software

## ዜናዊ መግለጫ

# ነፃው ግዕዝኤዲት ገጽ በጉግል ዓማርኛ መፈለጊያ

አብሻ/ኢኮሶ ኩባንያ በዛሬው ቀን አዲስ የጉግል መፈለጊያ የግዕዝኤዲት ገጽ ውስጥ አቅርቧል። ይህም ግዕዝኤዲት ገጽ በዓማርኛ በነፃ የሚያስከትብ [ኤችቲቲፒ://ፍሪታይፒንግ.ግዕዝኤዲት.ኮም](http://freetyping.geezedit.com) ወይም [http://freetyping.geezedit.com](http://freetyping.geezedit.com) በሚባል ድረገጽ ውስጥ ይገኛል።

አብሻ በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. በዶ/ር ኣበራ ሞላ እና ባለቤታቸው ወ/ሮ ሡናይት ከተማ የተቋቋመ ድርጅት ነው። ይህ የኮሎራዶ ተቋም ግዕዝን በኮምፒዩተር መጠቀም እንዲቻል መፍጠሩንና ሞዴት የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያን በ፲፱፻፹ ዓ.ም. ለዶስ ኮምፒዩተር ማቅረቡ ይታወሳል። ግዕዝን በኮምፒዩተር መክተብ በዶ/ር ኣበራ ከመጀመሩ በፊት ፊደሉ የሚጻፈው በእጅ ወይም ማተሚያ ቤቶች ብቻ ነበር። የኣብሻ ዘዴ በመባል በታወቀው በኣሁኑ ኣዲስ ፈጠራ ብዛታቸው ከ፫፻፴፫ በላይ የሆኑት የግዕዝ ፊደላት እያንዳንዳቸው የሚከተቡት እንደ እንግሊዝኛው ኣጻጻፍ ዓይነት ኣንድ ወይም ሁለት መርገጫዎች ብቻ በመጠቀም ነው።

ይኸንኑ መክተቢያ ሕዝቡ በነፃ እንዲጠቀምበት ኩባንያው ባላፈው ጥቅምት ድረገጹን በነፃ ማቅረቡ ይታወሳል። ድረገጽ ላይ በነፃ የግዕዝኤዲት ገጽ ለመጠቀም በጣም ቀላል ሊሆን የቻለው እያንዳንዱን ፊደል ከሁለት መርገጫዎች ባልበለጡ የሚያስከትብ የባለቤትነት መብቱ (ፓተንት / Patent) ሊሰጥ እየተጠበቀ ባለበት በኣዲስ ቴክኖሎጂ ላይ ስለተመረኰዘ ነው። ከድረገጽ ማንበብ የሚችል ማንም ተጠቃሚ በነፃ ከከተበ በኋላ ጽሑፉን ማረም፣ ማስቀመጥ፣ ማተምና ድረገጽም መሥራት የሚያስችል ውድና ኣዲስ ስጦታ ነው። ይህ ኣዲስ ግኝት ባይኖር የግዕዝ ተጠቃሚዎች ኣንዳንዶቹን ፊደላት ወይም ቅርጾች የሚከትቡት ከሦስት እስከ ስድስት መርገጫዎች በመጠቀምና ዋየሎች ላይ ያሉትንና ኣንዳንዶቹንም ለመድገም ባዶ ስፍራን መጨመር ኣስፈላጊም ነበር። ኣሁን ግን ማንኛውንም የግዕዝ ፊደል፣ ኣኃዝ፣ ምልክትና ማዜሚያ ለመክተብ ከሁለት መርገጫዎች በላይ መጠቀም እንዳላስፈለገ ይታወሳል።

በሚሸጠው ግዕዝኤዲት በግዕዝ መፈለግ ኣስቸጋሪ ኣይደለም። ነፃው የግዕዝኤዲት ገጽ ውስጥ ግን በኣዲሱ የጉግል መፈለጊያ ለመጠቀም “Search” የሚለውን በመጫን የጉግል መፈለጊያ ሳጥን ይወጣል። መስመሩ ውስጥ በተለመደው የግዕዝኤዲት ኣከታተብ መጠቀም ዓማርኛውን ያስከትባል። ከእዚያም ከቀኝ የሚገኘውን “Search” መጫን ጉግል የሚያውቃቸውን የዓማርኛ ጽሑፎች ዝርዝር ያስቀርባል። የሚፈለገውን መርጦ መጫን ጽሑፉን ይከፍታል። በጉግል ግዕዝኤዲት ገጽ ውስጥ በእንግሊዝኛ ለመፈለግ “Alphabet/ፊደል” ከእዚያም “Latin/ላቲን” የሚለውን መርጦ መጫን የሚፈለገውን ቃል ወይም ቃላት ሳጥኑ ውስጥ በእንግሊዝኛ የማስከተብና መፈለግ ምርጫ ይሰጣል።

ለተጨማሪ መረጃ [ግዕዝኤዲት.ኮም](http://geezedit.com) ወይም [ኢትዮፒክ.ኮም](http://ethiopic.com) ድረገጾች መጎብኘትና ኢ-ሜይልም [ለኢትዮጵያዊው@ኤኦኤል.ኮም](mailto:) ወይም [ግዕዝኤዲት@ኤኦኤል.ኮም](mailto:) መላክ ይቻላል። ኣድራሻው የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር Ethiopian Computers & Software, 10145 E. 143 Way,

**Thornton, CO 80602, USA አሜሪካ ሲሆን የስልክ ቍጥሩ 1-303-835-8025 ነው።**

*ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. ጀምሮ ግዕዝ በኮምፕዩተር እንዲከተብ የፈጠረ!*

